ሰዎች የትንሳኤ ቀን ባዶ እግራቸውን፣ ራቁትና ያልተገረዙ ሆነው ይሰበሰባሉ።

ከአማኞች እናት ዓኢሻህ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- እንደተላለፈው እንዲህ ብላለች: «የአላህ መልክተኛን -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፦ "ሰዎች የትንሳኤ ቀን ባዶ እግራቸውን፣ ራቁትና ያልተገረዙ ሆነው ይሰበሰባሉ።" እኔም "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ወንዶችም ሴቶችም ባጠቃላይ ከፊሉ ወደ ከፊሉ እየተመለከተ?" አልኳቸው። ነቢዩም -
የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - "ዓኢሻህ ሆይ! ጉዳዩኮ ከፊሉ ወደ ከፊሉ ከመመልከትም በላይ በጣም ከባድ ነው።" አሉኝ።»
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - የትንሳኤ ቀን የሚከሰተውን አንድ ክስተት እንዲህ በማለት ገለፁ። ሰዎች ለሒሳብ ከቀብራቸው ከተቀሰቀሱ በኋላ ያለ ጫማ በባዶ እግራቸው፣ ያለልብስ ሰውነታቸው ተራቁቶና እናታቸው እንደወለደቻቸው ቀን ያልተገረዙ ሆነው ይሰበሰባሉ። ይህንንም የአማኞች እናት ዓኢሻ -አላህ መልካም ስራዋን ይውደድላትና- ስትሰማ ተደንቃ እንዲህ አለች: "የአላህ መልክተኛ ሆይ! ወንዶችም ሴቶችም ባጠቃላይ ከፊሉ ወደ ከፊሉ እየተመለከተ?" ነቢዩም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - ከሞት መቀስቀስ በኋላ የመሰብሰብና የመቆም ጉዳይ ሀፍረተ ገላን ከመመልከትም በላይ የሰዎችን ሃሳብና አይን የሚሰልብ አስደንጋጭነት እንዳለው ገለፁ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5460